የፌዴራል ጤና ሚኒስቴር

# ሀገር አቀፍ የቅድመ-ጤና ተቋም ድንገተኛ ህክምና አምቡላንስ አገልግሎት አሰጣጥ መምሪያ




ሰኔ 2012 ዓ.ም

# Table of Contents


መቅድም ........ 2

መግቢያ ........ 4

ክፍል አንድ ........ 6

ጠቅላላ ድንጋጌዎች ........ 6

1. አጭር ርዕስ ........ 6

2. ትርጓሜ ........ 6

3. ***የመመሪያው መሻሻል አስፈላጊነት*** ........ 7

4. ***ዓላማ*** ........ 7

ክፍል ሁለት ........ 7

ክፍል ሦስት ........ 8

3. የቅድመ ጤና ተቋም አገልግሎት አምቡላንስ አጠቃቀም ........ 8

ክፍል አራት ........ 9

4. የባለ ድርሻ አካላት ተግባር እና ሃላፊነት ........ 9

1. የፌዴራል ጤና ሚኒስቴር ተግባርና ሀላፊነት ........ 9

2. የክልል ጤና ቢሮዎች ተግባርና ሀላፊነት ........ 10

3. የዞን ጤና መምሪያ ተግባርና ሀላፊነት ........ 10

4. የወረዳ ማስተዳድር ተግባርና ሀላፊነት ........ 11

5. የወረዳ ጤና ጽ/ቤት ተግባርና ሀላፊነት ........ 11

ክፍል አምስት ........ 12


DRAFT

5. የማጠረታቻ እና የውሎ አበል አከፋፈል ሥርዓት.................................................12

## መቅድም

የፌዴራል ጤና ሚኒስቴር(ሚ/ር) የሀገሪቷን ጤና ሥርዓት ለማሻሻልና ጥራቱን የጠበቀ አገልግሎት ለህብረተሰቡ ለማዳረስ ቀዳሚውን ድርሻ እየተጫወተ ይገኛል፡፡ ከዚህም ውስጥ ከእናቶችና ህጻናት፣ድንገተኛ አደጋዎችና አጣዳፊ ህመሞች የተያያዘ ሞትና አካለጎዶሎነት ለመቀነስ ይቻል ዘንድ በአዲስ መልክ የድንገተኛ ህክምና አገልግሎት በማደራጀት በጤና ድርጅቶችና በቅድመ ጤና ተቋም እና የአምቡላንስ አገልግሎት ከ2001 ዓ/ም ጀምሮ የተለያዩ ስራዎች ተግባራዊ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡ በዚህም መሰረት እ.ኤ.አ በ2015 ዓ.ም የተጠናቀቀውን የምእተ አመቱ ግብ የሆነው የእናቶችንና የህጻናትን ሞት ለመቀነስ አይነተኛ መፍትሄ እንዳለው በማሰብ በሀገሪቱ ላሉ ለሁሉም ወረዳዎች እንዲዳረስ ከከተማ ከንቲባዎችና ከክልል ፕሬዚደንቶች ጋር ስለአምቡላንስ አጠቃቀም የጋራ መግባቢያ ሰነድ በመፈራረም በተለያዩ ዙሮች ከ3000 የሚበልጡ አምቡላንሶችን ገዝቶ አሰራጭቶ ቀላል የማይባል ውጤትም አስገኝቷል፡፡

በተጨማሪም አምቡላንሶች ማናቸውንም ድንገተኛ ህመም የተፈጥሮ ሆነ ሰው ሰራሽ አደጋ ላጋጠማቸው ዜጎች የህይወት አድን እርዳታ እየሰጡ ተጎጂዎች ዘላቂ ህክምና ወደሚያገኙበት ጤና ተቋም እንዲያደርሱ የታለመለት ሲሆን ይህንንም በሰለጠኑ ባለሙያዎች የታገዘ ለማድረግ የድንገተኛ ህክምና ቴክኒሽያኖች (Emergency medical technician) በጤና ሳይንስ ኮሌጆች እያሰለጠነ ይገኛል፡፡

ከላይ የተጠቀሱትን አገልግሎቶች በጥራትና መዋቅሩን በተከተለ መልኩ ለማካሄድ ሀገር አቀፍ የቅድመ ሆስፒታል ድንገተኛ ህክምናና የአምቡላንስ አገልግሎት አሰጣጥ መመሪያ በ2006 ዓ/ም የተዘጋጀ ሲሆን ሁሉም የሚመለከታቸው አካላት እንዲተገብሩት በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ድጋፍና ክትትል ሲደረግበት ቆይቷል፡፡ መመሪያው በድንገተኛ ህክምናና አምቡላንስ አገልግሎት አወቃቀርና ፍሰት፣ በባለድርሻ አካላት ሀላፊነት እንዲሁም በሰው ሀይል አስተዳደር እና በድጋፍና ክትትል ሂደት ላይ ትኩረት የሰጠ

ሲሆን አሁን ካለንበት ደረጃና እንዲሁም በትግበራ ያጋጠሙ ተግዳሮቶችን መፍትሄ ከመስጠት አንጻር በ2012ዓ.ም እንዲሻሻል ተደርጓል፡፡ ይህ የተሻሻለው መመርያ ወቅቱን ያገናዘበና ከዚህ በፊት ከሚሰጣቸው አገልግሎቶች በተጨማሪ በአገራችን በከፍተኛ ደረጃ የሞትና ህመም መንስኤ የሆኑትን ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎችና የሰው ሰራሽና ተፈጥሯዊ አደጋዎች ምላሽ አሰጣጥ በተሻለ መልኩ ተደራሽ ከማድረግ አንጻር ጭምር የተሰራ በመሆኑ በየደረጃው ያሉ የስራ ሀላፊዎችና በአምቡላንስ ላይ የሚሰሩ ሰራተኞች መመርያውን በአግባቡ በመረዳትና በመተግበር ሀላፊነታቸውንና ተጠያቂነታቸውን ለመወጣት የሚያግዝ መመርያ ነው፡፡

ይህን እድል ተጠቅሜ ለዚህ መመሪያ መሻሻል ዝግጅት ላይ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ላበረከቱ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት ከፍ ያለ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

ዶ/ር

DRAFT

## መግቢያ

በሀገራችን ኢትዮጵያ የቅደመ ጤና ተቋም ድንገተኛ ህክምና አምቡላንስ አገልግሎት በኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ማህበር አማካኝነት በ1944ዓ.ም በአዲስ አበባ በነጻ የአምቡላንስ አገልግሎት በመስጠት የተጀመረ ሲሆን በአሁኑ ጊዜ አገልግሎቱ በመስፋት በመንግስት፤ በተለያዩ የግልና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች አገልግሎቱ በመሰጠት ላይ ይገኛል፡፡ በዓለም ጤና ድርጅት መረጃ መሰረት በማደግ ላይ ያሉ አገሮች የቅድመ ጤና ተቋም ድንገተኛ የአምቡላንስ አገልግሎት ሥርአታቸውን በማሻሻል በእናቶችና ህጻናት፤ከአደጋ ጋር እና ከተለያዩ አጣዳፊ ህመሞች በተያያዘ የሚደርሰውን ሞትና አካለ ጎደሎነት ከ25-50% መቀነስ እንደሚቻል ስለሚመክር ሀገራችንም ይህ አገልግሎት ተጠናክሮ እንዲቀጥል ከ2001ዓ/ም ጀምሮ የተለያዩ ስራዎችን በማከናወን ላይ ትገኛለች፡፡ከነዚህም ውስጥ በከፍተኛ ደረጃ ዘርፉን መምራት የሚችሉ የድንገተኛ ህክምና ሃኪሞችና ነርሶች ማሰልጠን፤ቀጥታ በአምቡላንስ ውስጥ እርዳታ የሚሰጡ የድንገተኛ ህክምና ቴክኒሽያኖች፤አደጋው ወይም አጣዳፊ ህመም በደረሰ ጊዜ በቦታው የመጀመሪያ ህክምና እርዳታ መስጠት የሚችሉ የህብረተሰብ አካላት /CFAR/ ማሰልጠን፤ በተለያየ ዙር ከ3000 በላይ የሚሆኑ አምቡላንሶች ግዢ በማካሄድና በማከፋፈል የአምቡላንስ ስርጭት 1:25000 ለማድረስ ከፍተኛ ጥረት ተደርጎ አበረታች ውጤት አስገኝቷል፡፡

ሆኖም የተሰራጩት አምቡላንሶች ከትራንስፖርትነት የዘለለ አገልግሎት ባለመስጠታቸው፣የህዝብ ቁጥር መጨመር፣ የከተሞች እድገት መስፋፋት፣ የህዝብ አኗኗር ዘይቤ መቀየር፣ የትራንስፖርት፣ የኢንዱስትሪዎች እንዲሁም የመሰረተ ልማት ግንባታዎች መስፋፋት አገሪቷን ለተለያዩ አዳዲስ በሽታዎችና አደጋዎች ተጋላጭ ሊያደርጋት ስለሚችል ተመጣጣኝ ምላሽ የሚሰጥ የቅድመ ጤና ተቋም የአምቡላንስ አገልግሎት ሥርአት መዘርጋት አስፈልጓል፡፡

በቀጣይ የአምቡላንስ አገልግሎቱ ተጎጂዎችን በፍጥነት ከማድረስ በተጨማሪ ጉዳተኞችን አደጋ ወይም ህመም ከደረሰባቸው ቦታ ጀምሮ ደረጃውን የጠበቀ ተገቢውን እርዳታ እያገኙ ወደ ጤና ድርጅት የሚደርሱበት፤በተጨማሪም ተደራሽ ለማድረግ የግንኙነት መረብን እንደየአካባቢው ሁኔታ በማደራጀት የአምቡላንስ ጥሪ ምላሽ ጊዜን (Emergency Response Time) ለማሻሻል ና የአምቡላንስ ስርጭት 1:25000 ለማድረስ መንግስት ጥረት እያደረገ ይገኛል፡፡

ከላይ የተጠቀሱትንና መሰል ሁኔታዎች መነሻ በማድረግ እና በነባሩ መመርያ ላይ የታዩ ክፍተቶችን በማስተካከል የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፓብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣዉ አዋጅ ቁጥር 691/2003 መሰረት የፌዴራል ጤና ሚኒስቴር ችግሩን በዘላቂነት ለመቅረፍ እንዲያስችል የአምቡላንስና ድንገተኛ ህክምና አገልግሎትን በተጠናከረና በተደራጀ መልኩ በሀገር አቀፍ ደረጃ ለማዋቀር ይህ መመሪያ ተሻሽሏል፡፡

DRAFT

## ክፍል አንድ

### ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. **አጭር ርዕስ** - *ይህ ሀገር አቀፍ የቅድመ-ጤና ተቋም ድንገተኛ ህክምናና አምቡላንስ አገልግሎት አሰጣጥ መምሪያ ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡*

2. **ትርጓሜ**
    1. ***የቅድመ ጤና ተቋም ድንገተኛ ህክምናና አምቡላንስ አገልግሎት፡-*** ማንኛውም ሰው አጣዳፊ የጤና እክል ሲያጋጥመው ያለ ምንም ልዩነት ችግሩ በደረሰበት አካባቢ ባሉ የሰለጠኑ የማህበረሰብ *መጀመሪያ* ህክምና እርዳታ ሰጪዎች እርዳታ በመስጠት ለቀጣይ የተሻለ አገልግሎት የአደጋ ጥሪ ማዕከል በመደወል አፋጣኝ በህክምና ቁሳቁስና በሰለጠነ የሰው ሃይል የተደራጀ አምቡላንስ እንዲደርስ በማድረግ ያልተቆራረጠ እርዳታ በመስጠት ወደ ጤና ድርጅት ማድረስ ማለት ነው፡፡
    2. ***ድንገተኛ ህመም ወይም አደጋ፡- የሚባሉት*** ምጥ ላይ ለምትገኝ ነፍሰጡር ሴት፣በእርግዝና ላይ ሆና ማንኛውም አይነት አጣዳፊ ህመም ላይ ለሆነች ሴት፣ማናቸውም የህጻናትና የአዋቂ ድንገተኛ እና አጣዳፊ የሆነ ህመም፣ በተፈጥሮ በመኪና በእሳት ወይም በማናቸውም ሰው ሰራሽ በሆነ አደጋ ሲከሰት እንዲሁም ህዝባዊ መድረኮች በሚኖሩበት ጊዜ እንደ የዝግጁነት (standby) አገልግሎት ያካትታል፡፡
    3. ***የጥሪ ማዕከል፡-*** *ማንኛውም ዓይነት የድንገተኛ አደጋ ወይም ህመም በሚኖርበት ጊዜ ጥሪዎች የሚስተናገዱበት እና መረጃዎችን የሚያደራጅ ማዕከል ሆኖ በቀላሉ ሊያዝ የሚችል ሀገር አቀፍ የሆነ ባለሶስት ዲጂት የጥሪ መቀበያ ቁጥር ይኖረዋል፡፡*
    4. ***የስምሪት ማዕከል፡-*** *ከድንገተኛ ጥሪ ማዕከል በሚቀበለው ጥሪ መሰረት በስሩ የሚገኙ አምቡላንሶችን የሚያሰማራና መረጃዎችን የሚያደራጅ ማዕከል ነው፡፡*
    5. ***ገጠር እና የገጠር ከተማ፡-*** *በዚህ መምሪያ መሰረት ከክልል ከተሞች ውጪ የሚገኙትን ገጠርና የገጠር ከተሞችን ያጠቃልላል፡፡*
    6. ***ከተማ፡-*** *በዚህ መምሪያ መሰረት የክልል ከተሞችንና ከተማ መስተዳደሮችን ያጠቃልላል፡፡*

DRAFT

### 3. የመመሪያው መሻሻል አስፈላጊነት

በሥ ላይ የሚገኘው የቅድመ ጤና ተቋም የአምቡላንስ አገልግሎት መመሪያ ለማስፈጸም የተለያዩ ክፍተቶች ያሉበት መሆን፤ የአምቡላንስ የፋይናንስና በጀት አጠቃቀም ግልጽ አለመሆን፤ ክልሎች የቅድመ ጤና ተቋም የድንገተኛ ህክምና አገልግሎትን በወጥነት እየተገበሩት ባለመሆኑ በአገልግሎቱ ላይ የሚፈለገውን ውጤት ማምጣት ባለመቻሉ የጤና ሚኒስቴር የነባሩ መመሪያ ክፍተቶችን ለመሙላት እና ወቅቱ የሚጠይቀውን አገልግሎት እንዲኖር ለማድረግ ይህ መመሪያ እንዲሻሻል አድርጓል፡፡

### 4. ዓላማ

ድንገተኛ አደጋ እና ህመም የደረሰባቸው ሰዎች ተገቢውን የቅድመ ጤና ተቋም ድንገተኛ ህክምናና አምቡላንስ አገልግሎት ቀጣይነትና ወጥነት ባለው መልኩ እንዲያገኙ ሥርዓት መዘርጋት ነው፡፡

### 5. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በሃገሪቱ ውስጥ በቅድመ ጤና ተቋም ድንገተኛ ህክምናና አምቡላንስ አገልግሎት ለሚሰጡ የመንግስት እና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት ተግባራዊ ይሆናል፡፡

# ክፍል ሁለት

## 2. የቅድመጤና ተቋምድንገተኛ ህክምና አምቡላንስ አገልግሎት አደረጃጀት

2.1 በአገራችን ካለው የመልክአ ምድር ስፋት፣የቴክኖሎጂ እድገት እና የህብረተሰቡን ፍላጎት መሰረት ባደረገ መልኩ የቅድመ ጤና ተቋም ድንገተኛ ህክምናና አምቡላንስ አገልግሎት በገጠር እና በከተማ በሁለት የተለያየ መልክ ይደራጃል፡፡

2.2 በገጠር ደረጃ የቅ/ጤ/ተ/ድ/ህ/አምቡላንስ አገልግሎት አደረጃጀት

2.3 በገጠር እና ገጠር ከተሞች የቅ/ሆ/ድ/ህ/አምቡላንስ በበላይነት በወረዳው ጤና ፅህፈት ቤት ይመራል

2.4 በገጠር እና ገጠር ከተሞች የቅ/ሆ/ድ/ህ/አምቡላንስ አገልግሎት ለመስጠት አንድ የጥሪ እና የስምሪት ማዕከል በመልክአ ምድር ስፋት እና ህዝብ ብዛት በወረዳው ጤና ፅህፈት ቤት ይደራጃል

2.5 በገጠር እና ገጠር ከተሞች የአምቡላንሶች መቀመጫ /station/ በጤና ጣቢያ ላይ መሆን አለበት

2.6 በከተማ እና በከተማ አስተዳደር የቅ/ሆ/ድ/ህ/አምቡላንስ አገልግሎት አደረጃጀት

2.7 በከተማ እና በከተማ አስተዳደር የቅ/ጤ/ተ/ድ/ህ/አምቡላንስ በበላይነት በከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮ እና ፅህፈት ቤት ይመራል

2.8 በከተማ እና በከተማ አስተዳደር የቅ/ሆ/ድ/ህ/አምቡላንስ አገልግሎት ለመስጠት አንድ የጥሪ እና የስምሪት ማዕከል በከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮ እና ፅህፈት ቤት ያደራጃል

2.9 በከተማ እና በከተማ አስተዳደር የአምቡላንሶች መቀመጫ /station/ ለአደጋ ተጋለጭነት እና የህዝብ ብዛት ታሳቢ ባደረገ መልኩ የከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮ እና ፅህፈት ቤት ያደራጃል

## ክፍል ሦስት

### 3. የቅድመጤና ተቋምአገልግሎት አምቡላንስ አጠቃቀም

1. የድንገተኛ ጥሪ ካልደረሰው በስተቀር አምቡላንሱ በምንም አይነት መልኩ ከአምቡላንሶች መቀመጫ /station/ መንቀሳቀስ አይችልም
2. አምቡላንስ ታካሚዎችን /ተጎጂዎችን ለማንቀሳቀስ አገልግሎት ብቻ መዋል አለበት

DRAFT

3. የአምቡላንስና ድንገተኛ ህክምና አገልግሎት በነጻ ይሰጣል
4. የትራፊክ አደጋ ለሚሰጥ አገልግሎት የአምቡላንስና ድንገተኛ ህክምና አገልግሎት ወጪ በሶስተኛ ወገን ይሸፈናል
5. የጤና ባለሙያ ወይም የድንገተኛ ህክምና ቴክኒሽያን ከታማሚው አጠገብ እርዳታ እየሰጠ መሄድ አለበት
6. ከአንቡላንስ ጋር ከተገልጋይ በተጨማሪ አንድ አስታማሚ ብቻ በአምቡላንሱ ጋቢና ከሾፌር አጠገብ ሆኖ መሄድ ይችላል
7. ከእያንዳንዱ አገልግሎት በኋላ አምቡላንሱ በተገቢ ሁኔታ በሽታ አምጭ ተህዋስያንን ለመከላከል በስታንዳርድ መሰረት መጸዳት አለበት
8. አምቡላንሱ አስፈላጊው ጥገና በተገቢው ጊዜ ተደርጎለት ሁልጊዜ ለአገልግሎት ዝግጁ መሆን አለበት

# ክፍል አራት

## 4. የ ባለ ድርሻ አካላት ተግባር እና ሃላፊነ ት

### 1. የ ፌዴራል ጤና ሚ ኒስቴር ተግባርና ሀላፊነ ት

i. የቅድመ ጤና ተቋም ድንገተኛ ህክምናና አምቡላንስ አገልግሎት ሥርዓትን የሚመለከት መመሪያ ያዘጋጃል፤እንደአስፈላጊነቱ ማሻሻያ ያደርጋል
ii. የዚህን መመሪያ አተገባበር ከክልል ጤና ቢሮዎች ጋር በመሆን ይከታተላል
iii. የቅድመ ጤና ተቋም ድንገተኛ ህክምናና አምቡላንስ አገልግሎት አሰጣጥ ላይ የሚሳተፉ የባለድርሻ አካላትን ይለያል፤ ያስተባብራል
iv. በአለም ጤና ድርጅት ስታንዳርድ መሰረት የአምቡላንስ ለህዝብ ጥምርታ 1:25000 እንዲሆንና አቅርቦትን ማረጋገጥ

DRAFT

v. የድንገተኛ ህክምናና አምቡላንስ አጠቃቀም በተመለከተ የህብረተሰቡን ግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን ይሰራል
vi. እንደአስፈላጊነቱ የስራ ላይ የአቅም ግንባታ ስልጠና ይሰጣል፡፡
vii. የቅድመ ጤና ተቋም ድንገተኛ ህክምናና አምቡላንስ አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል

## 2. የክልል ጤና ቢሮዎች ተግባርና ሀላፊነት

i. የክልሉን የቅድመ ጤና ተቋም ድንገተኛ ህክምናና አምቡላንስ አገልግሎት መመሪያን ያስተገብራል
ii. የክልሉን የቅድመ ጤና ተቋም ድንገተኛ ህክምናና አምቡላንስ አገልግሎት ሀይል ያደራጃል
iii. ለድንገተኛ ህክምና ቴክኒሽያኖች መደበኛ ስልጠና እንዲሁም የስራ ላይ የአቅም ግንባታ ስልጠና ይሰጣል፡፡
iv. የክልሉን የቅድመ ጤና ተቋም ድንገተኛ ህክምናና አምቡላንስ አገልግሎት ግብአት መሟላቱን ያረጋግጥል፤ይደግፋል
v. የክልሉን የቅድመ ጤና ተቋም ድንገተኛ ህክምናና አምቡላንስ አገልግሎት አስተዳደርን የክልሉ ጤና ቢሮ የክልሉን ምክር ቤት አስወስኖ ለሶስተኛ ወገን ማስተላለፍ ይችላል
vi. ስለቅድመ ጤና ተቋም ድንገተኛ ህክምናና አምቡላንስ አጠቃቀም ለህብረተሰቡ ግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን ይሰራል
vii. የክልሉን የቅድመ ጤና ተቋም ድንገተኛ ህክምናና አምቡላንስ አገልግሎት አሰጣጥ ላይ የህዝብ ተሳትፎ እንዲጎለብት ያደርጋል
viii. የክልሉን የቅድመ ጤና ተቋም ድንገተኛና አምቡላንስ አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ድጋፍ እና ክትትል ያደርጋል

## 3. የዞን ጤና መምሪያ ተግባርና ሀላፊነት

i. በዞኑ የቅድመ ጤና ተቋም ድንገተኛ ህክምናና አምቡላንስ አገልግሎት መመርያውን ያስፈጽማል

DRAFT

ii. የዞኑን የቅድመ ጤና ተቋም ድንገተኛ ህክምና አምቡላንስ አገልግሎት አሰጣጥ ለክልል ጤና ቢሮ ሪፖርት ይልካል
iii. በዞኑ ውስጥ ባሉ ወረዳዎች መደበኛ በጀት ለቅድመ ጤና ተቋም ድንገተኛ አምቡላንስ አገልግሎት ይመድባል/ ያስመድባል
iv. በወረዳዎች የሚታዩ ምርጥ ተመክሮዎችን ያስፋፋል
v. ስለቅድመ ጤና ተቋም አምቡላንስ እና ድንገተኛ ህክምና አጠቃቀም የህብረተሰቡን ግንዛቤ እንዲጎለብትና የህብረተሰቡ ተሳትፎ እንዲኖር ያደርጋል
vi. የቅድመ ጤና ተቋም ድንገተኛ ህክምናና አምቡላንስ አገልግሎት አሰጣጥ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል

## 4. የወረዳ ማስተዳድር ተግባርና ሀላፊነት

i. በወረዳው የጤና ፅ/ቤት የቅድመ ጤና ተቋም ድንገተኛ ህክምናና አምቡላንስ አገልግሎት መመሪያ አተገገባበርን ይከታተላል
ii. ለወረዳው ጤና ፅ/ቤት ለቅድመ ጤና ተቋም ድንገተኛ ህክምናና አምቡላንስ አገልግሎት በጀት ይመድባል
iii. በወረዳው የቅድመ ጤና ተቋም ድንገተኛ ህክምናና አምቡላንስ አገልግሎት እንዳይቋረጥ ያደርጋል
iv. ለድንገተኛ ህክምና ቴክኒሽያኖች  የስራ ላይ የአቅም ግንባታ ስልጠና ይሰጣል፡፡
v. ለአምቡላንስና ድንገተኛ ህክምና አገልግሎት የተመደበውን አምቡላንስ ከታለመት አላማ ውጪ እንዳይውል ይከታተላል፤
vi. ስለድንገተኛ ህክምናና አምቡላንስ አጠቃቀም የህብረተሰቡን ግንዛቤ እንዲጎለብትና የህብረተሰቡ ተሳትፎ እንዲኖር ያደርጋል

## 5. የወረዳ ጤና ጽ/ቤት ተግባርና ሀላፊነት

i. የቅድመ ጤና ተቋም ድንገተኛ ህክምና አምቡላንስ አገልግሎት መመሪያን ይተገብራል
ii. የቅድመ ጤና ተቋም አምቡላንስና ድንገተኛ ህክምና አገልግሎት አመታዊ እቅድ ያዘጋጃል ይተገብራል

iii. የአምቡላንስ የጥሪ እና ስምሪት ማዕከል ያቋቁማል፣ያስተዳድራል

iv. የአምቡላስ መቀመጫ /station/ ያቋቁማል፤ ያስተዳድራል

v. ለቅድመ ጤና ተቋም ድንገተኛ ህክምና አምቡላንስ አገልግሎት የሚያስፈልጉ በቂ የሰው ሀይል ይቀጥራል፤ ያስተዳድራል

vi. ለቅድመ ጤና ተቋም ድንገተኛ ህክምና አምቡላንስ አገልግሎት የሚያስፈልጉ ግብአቶችን ያሟላል

vii. የአምቡላንስ ተሽከርካሪዎች መደበኛ ጥገና እንዲያገኙ ያደርጋል

viii. በወረዳው የቅድመ ጤና ተቋም ድንገተኛ ህክምና አምቡላንስ አገልግሎት ላይ የህብረተሰብ ተሳትፎ እንዲኖር ያደርጋል

ix. የቅድመ ጤና ተቋም አምቡላንስ ድንገተኛ ህክምና አገልግሎት ላይ የግንዛቤ ማስጨበጭ ስራዎችን ይሰራል

x. የቅድመ ጤና ተቋም ድንገተኛ ህክምና አምቡላንስ አገልግሎት አፈፃጸም ሪፖርት ለሚመለከተው አካል ይልካል

## ክፍል አምስት

### 5. የማበረታቻ እና የውሎ አበል አከፋፈል ሥርዓት

i. ለድንገተኛ ህክምና አገልግሎት ባለሙያዎች የተጋላጭነት ክፍያ በወር 470ብር ይከፈለዋል

ii. ለድንገተኛ ህክምና አገልግሎት ባለሙያዎች የትርፍ ሰዓት በጤና ባለሙያዎች አከፋፈል እስኬል መሰረት ይከፈላቸዋል

**የጤና ሚ/ር ይህን መመሪያ እያየ ሊያሻሽል ይችላል።**